# መደነብ ወይስ መደመር

**ውድ ወገኖቼ ይህንን ጽሁፍ ስጽፍ ዝም ብዬ ለመቃወም አይደለም።እኔ በዚህ ለውጥ ውስጥ ተጠቃሚ ነኝ ምክንያቱም የ 18 ዓመታት ፍርደኛ የነበርኩና አሁን ግን የተነሳልኝ በመሆኑ ይህንን ሥራዓት በመደገፍና ሀገሬ መግባት የምናፍቅ ዜጋ ነኝ። ሀገሬን የለቀቅኩ 18 ዓመታት ከተፈርደብኝ በኋላ ነው።ከቃሊቲ በ 5000 ብር ዋስ ከተለቀቅሁ በኋላ ለሁለት ቀጠሮ ከቀረብኩ በኋላ እንደምታውቁት ፍርድ ቤቱ እንደሚፈርድብኝ ጥርጥር ስላልነበረኝ ከአዲስ አበባ ከተማ ሲዳሞ ክፍለሀገር ውስጥ እርጋጨፌ እና ሀገረማሪያም መካከል ላይ የምትገኝ ገደብ የምትባል ከተማ እራሴን ደብቄ ከአንድ ዓመት ከአንድ ወር በላይ ከተቀመጥኩ በኋላ ነበር ሀገሬ እንድለቅ የተገደድኩ።ይህን ጽሁፍ ስጽፍ በቅን ኢትዮጵያዊነት ስለሆነ በሰከነ መንገድ ተመልከቱት። ሁል ጊዜ ሥራዓት ሲለውጥ የህዝብን ፍላጎት በማንሳት የህዝብን ስሜት በቆጣጠር እንደሆነ ብያንስ የፋሺስቱ ደርግንና የትግሬዎችን ነጻ አውጭዎች ሲመጡ ያሉንን እናስታውስ።**

**ደርግ፡ "ያለምንም ደም እንከኗ ይውደም" በኋላ ግን "አብዮት ልጇን ትበላለች" እስኪ ልብ በሉ ደርግ ያጠፋው ተቋዋሚዎችን ብቻ ሳይሆን አጥናፉ አባተንና ሌሎችን ውድ የኢትዮጵያንን ጀነራሎችን ነበር።**

**የትግሬዎች መንግስት፡** " ብሶት የወለደው ኢህአዴግ የደርግ መጠቀሚያ የሆኑትን ሁሉ ተቆጣጠረ" በኋላስ ብሶት ያለበትን ሕዝብ " የደርግ ናፋቂ እና አሸባሪ በማለት" በአደባባይና በስውር የፈጀውን ቤት ይቁጠረው።

ወገኖቼ ሆይ "ካለ መድሃኒዓለም በስተቀር የሚታመን ማን ነው!!!" የምንል ኢትዮጵያዊያን ዛሬ ያለምንም መተማመኛ እንዴት ዶ/ር አብይን አመነው? የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ሆነ ነገሩ?

እስኪ እናስተውል የቅንጅት መክሸፍ ዋናው ነጻ የጦር ሃይልና ፖሊስ እጦት፣ ብዙኋን መገናኛ እጦት፣ ነጻ ፍርድ ቤት እጦት፣ነጻ ምርጫ ቦርድ እጦት መሆኑን እንዴት ዘነጋነው? ታዲያ ለነዚህ ለተወሰኑት ብቻ እንኳን የሺግግር መንግስት ለጊዜው አያስፈልገንም? ይህን ለሂሊናችሁ እተዋለሁ።

ውድ ወገኖቼ መደመር መደመር መደመር----ሆኗል;፡ በቅድሚያ ወደ መደመር ከማለፌ በፊት መደነብ ማለት ምን ማለት ነው? በከተሞች አካባቢ ከብቶቻቸውንና በጎቻቸውን ለሚጠብቅላቸው ሰው ሲያስረክቡ ደነቡ ይባላል። ነገርግን የሚደነቡት እንስሳ አባሰንጋም ይያዘው ሌላም በሺታ እረኛው አይመልስም ይቀበላል። አለበለዚያ ደሞዙን አያገኝማ። ዶ/ር አብይም እኔ የሚጨነቀው ስለዘላቂው ሳይሆን ለጊዜ በበላበት የሚጮሆውን ተቃዋሚ በሥሬ በማድረግ ግቤ እስክደርስ ከቆመታቸው በላይ አክብሮት በመስጠትና ወደኔ መሳብ ብለው ያቀዱት ብልጣ ብልጥነት ይሄው እየተሳካላቸው ይመስለኛል። ተቃዋሚ ነን የሚሉት "እግር እስከመሳም ደርሰዋል" እውነት ይህ ከቅን ልብ የተደረገ ነው?እንግዲህ ተቃዋሚዎች ምን ያህል ትንሾችና አሳፋሪዎች እንደሆኑ ትለቁ ማሳያ ነው። ይህ ታዲያ መደነብ ወይስ መደመር?

ውድ ወገኖቼ "የነቶሎ ቶሎ ቤት ግርግዳው ሰንበሌጥ" እንደሚባል በስሜታዊነት የተገነባ ቤት ፈጥኖ እንደሚፈርስ አንድ ምሳሌ ላንሳላችሁ። ጌታችን አምላካችንናመንድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስን ይከተለው የነበረው አንድ ገብያ የሚያክል ህዝብ በጭንቋ ጊዜ እንዴት እንደሼሸው።እሱ ብቻ አይደለም ቅዱስ ጴጥሮስ እንኳን የራሱ ሃዋሪያት የምትሉትን ሰው አላውቀውም ነው ያለው።ታዲያ ስሜታዊነት የት ያደርሰን ይመስለናል?????????????????

ውድ ወገኖቼ እስኪ ቀድመው የገቡትን እና ወደፊት የሚገቡትን እነማን እንደሆኑ እናጢን፡-

1ኛ.የቀድሞ የኅ.ወ፣ሃ.ት መሪዎች ምን ነበር በኢትዮጵያዊነት የነበራቸው አቋም ?

*ሀ*.ማግቤት( ማህበሪ ግስግስ ቤሔሬ ትግራይ)፣ታ.ህ.ት መጨራሻም ህ.ወ.ሃ.ት በርሃ ሳይወጡ የሚያውጣቸውን ፓንፐሌት አቶ ገ.መድህን አርአያ እንዳጋለጡት፡-

1ኛ.**ስለ ኢትዮጵያ የነበራቸው አቋም**

- -ኤርትራ የኢትዮጵያ ቀኝ ግዛት ናት
- ኤርትራ ከኢትዮጵያ በፊት የሰለጠነች ሀገር ስትሆን ኢትዮጵያ ቅጂ ግዛት ያዘቻት
- ኢትዮጵያ በሚኒሊክ ጊዜ የተፈጠረች ሀገር ናት

  2ኛ. **ትግራይ ነፃ ሆና የኖረች ሀገር ናት**
- ትግራይ ነፃ ሉአላዊነቷን አስከብራ የኖረች ሀገር ስትሆን በሚኒሊክ የአማራው ቅኝ ገዥ ተውራ ቅኝ ግዛት ሆነች። ስለዚህ የትግራይ ህዝብን ከአማራው ቅኝ ግዛት አስወጥተን የትግራይን ሪፐብሊክ መመስረት አለብን።

- ❖ አማራ የሚባለው የትግራይ ሕዝብ ጠላት ነው።ጠላት ብቻ አይደለም የጠላት ጠላት ነው።ስለዚህ አማራን ማጥፋት አለብን።አማራ ካልጠፋ የትግራይን ሪፐብሊክን መመስረት አንችልም!!!

ኢትዮጵያ በሚኒሊክ የተፈጠረች ሀገር በመሆኗ መቶ /100/ ዓመት የማይሞላትና ብሔርና ብሔረሰቦችን በቅኝ ግዛት አጠቃል ከማያዟም በላይ ኢትዮጵያ የሚባለው ስም ከዚያ በፊት የማይታወቅ በመሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች ነፃ በመውጣትና የራሳቸው መንግስት መመስረት አለባቸው በማላት በማንፌስቶአቸው እንዳወጡት አቶ ገ/መድህን አጋልጠዋል። እስኪ የቀድሞ የኅ.ወ.ሃ.ት. አመራሮች ኤርትራና ትግራይ ቀደምቶች ከሆኑ ለምን መጽሐፍ ቅዱስ አልነበራችሁም? ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ከ45 ጊዜ በላይ ተጠቅሳለች ታዲያ እናንተ ጋ መጽሐፍ ቅዱስ አልደረሰም ነበር? ታዲያ አሁን ቃለ መጠይቅ ሲደረግላችሁ ይቅርታ መጠየቅ ወይስ መካድ ነበረባችሁ?
ይህንን ቪድዮ እንደገና ተመልከታችሁ የሂሊና ፍርድ ስጡ፡-

=Must-watch: Gebremedhin Araya Shares unheard TPLF secrets on ESAT (published on Dec 31.2011

የመጀመሪያው የኅ.ወ.ሃ.ት መሪዎች የሰጡትን ቃለመጠይቅ ይህ ነው ያደምጡት፡-

LTV/show-ሕዋሃት ምን ነበር? አሁንስ ምን እየሆነ ነው?( published on Aug 1, 2018.

## ለ. አቶ ታምራት ላይኔ

ትልቁ የአማራ ጠላት እንደሆኑ ይታወቃል። እስከአሁን ይቅርታ ጠይቀዋል?እዚህ ላይ የአማራው ጠላቶች ምን ያህል እየተሰባሰቡና ክብር እንዳገኙ ይቅርታ ለመጠየቅም አለመፈለጋቸው ምን ያህል ለአማራው አሳፋሪ መሆኑን ተመልከቱ፡-(NahooTV ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር ከአቶ ታምራት ላይኔ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ) ክፍል አንድ እና ክፍል ሁለት Aug1/2018

## ሐ. ባለሜንጫው

ባለ ሜንጫው ደግሞ ዛሬ እጅግ ክብር አግኝቶ በደስታ ላይ ይገኛል።ይህ ምን ማለት ነው።ፀረ አማራ መሆን በህግ አያስጠይቅም ወይም አማራ ለኢትዮጵያ ሁለተኛ ዜግ በመሆኑ ወይስ እሱን የበደሉ በሙሉ በመደመራቸው ይታለፋሉ?

## መ. ግንቦት ሰባትና ኢሳታቸው

በእውነት ግንቦት7 እና ኢሳት በአማራው ላይ ያደረሱት በደል እንዲህ በቀላል የሚታይ ነው?ግን በእነሱ አልፈርድም ቁልፍ የኢሳት አመራሮች፣ ገንዘብ ሰብሳቢዎችና ደጋፊዎች እነማን ሆኑና የአማራው ጠላት አማራ ነው።ጥቅም ከተገኘ እንኳን የወልቃይት አማራ መላው አማራ ቢያልቅ እነሱ ምን ቸገራቸው፤ምዕራባዊያን ካሉላቸው ማንን ፈረተው።

ጀግኖች ግንቦት7 ኢድያሚንንን ሆናዋል እኳ የነ ኮለኔን ታድሰ ሙሉነህን አርበኞች ግንባር ቀምተው በራሳቸው ላይ ጨምረው አርበኞች/ግንቦት7 ሲሆኑ ማን ከልካይ ነበረባቸው።ኮሌኔል በሂይወት ካለህ አንድ ቀን ጉድህን ታየዋለህ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" መሆኑን።

ወገኖቼ እባካችሁ ተደመሩ ተደመሩ የምንባለው እኛ ጥንትም ኢትዮጵያዊ ዛሬም ኢትዮጵያዊ ጠቅላይ እዬ እኛ እኮ አይደለንም እኮ " ኦሮሞ ፈርስት" የሚሉት ናቸው እኮ ተሳስተው ከሆነ በቅርብ ቀን እርሶ ጋ ይመጣሉ።ቢሳሳቱም አይፈረድቦትም በአሁኑ ጊዜ በኢሳት የተሾሙ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ስላሉ ነው፤ስለዚህ ወደፊት ሰከን ሲሉና ጊዜ ሲኖሮዎት ያውቋችኋል።

ጠቅላይ እዬ እኛ ድሮም የተደመርን በመሆናችን ትምክተኞች፣ነፍጠኞች፣ደርግን ናፋቂዎች እና የመሳሰሉት ሲለጠፉብን የኖሩት እኮ እንደምር ስላልናቸው ነው እኮ ረሱት? በደርግ ጊዜ "ፈጣን ነው ባቡሩ ፈጣን ነው ባቡሩ ፈጣን ያልሆናችሁ እንዳትሳፈሩ"ሲባል ፈጣን ነን ያሉ ፈጥነው ተሳፍረው ያገኙት ትርፍ "አብዬት ልጇን ትበላለች" ነው መጨረሻቸው የሆነ። እኛን እያሉን ያሉት ተደነቡ ከሆነ " እኛም አውቀናል ጉድጓድ ምሰናል" ነው መልሳችን። በአጠቃላይ ይቅርታ የሚሰራው የአስተዳደር በደል ለፈጸሙት እንጂ በጅምላ ሰዎችን ለጨረሱና ላስጨርሱም ከሆነ እንግዲ ይህን ምን ይሉታል? ወራጅ አለ ከማለት ውጭ።

ሌላው ደግሞ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለሁለት ተከፍላ እንደነበርች የምናውቀው ነው።ነገርግን ኢትዮጵያ ያሉት ብዙ ቁጥር ያላቸው የአህዛቡ የኅ.ወ.ሃ.ት ካድሬ ጳጳስ የሆኑበት ፤ቅባቶች፣ ተዋድሶዎች፣እንድሁም የሙሰኞች ዋሻ እንደነበረች ይታወቃል።የአሜሪካው ደግሞ የግንቦት7 ካድሬዎችና ተሃድሶዎች ጠንክረው የሚታዩባት

እንደነበረች ግልጽ ነው።ይህን ስል ፓትራይትኩና ጥቂት ቅን ጳጳሳት እንዳሉ ሃቅ ነው።ነገርግን ይህን ልዩነት ሳያስታርቁ እንዴት ተደመርን ይላሉ።ይህ ከላይ እንዳልኩት መደመር ሳይሆን መደነብ ነው የምለው።

አባቶቼ ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡-" መልካም እረኛ እኔ ነኝ።መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎች ያኖራል።እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ተኩላም ይነጥቃቸውል በጎቹንም ይበትናቸዋል።ሞያተኛ ስለ ሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል።"

ዲያቆን ዳንኤል አንተ ተደመሩ ትላለህ እኔ ግን ተደነቡ ነው የምለው የአምናውን አያድርገውና ቀድመህም የምትቃወመ አንተ ትሆን ነበር ታዲያ አሁንስ እንዴት ታየዋለህ?እንደው በአጋጣሚ ካነበብከው ወይም ሰዎች ከነገሩህ እንደው መልስ ብትሰጠኝ ደስ ይለኛል።

እንዲሁም የእስላሞችሁ ለረጅም ጊዜ የነበረው ትግል እውነተኛ መሪዎቻችን ታስረውና ታግደው የማንፈልገው "የሃበሽ" እምነት አስተምሮ ተጥሎብናል የሚሉት እንዴት ነው ዛሬ ተደመርን የሚሉት? ለካ በመደመር የማይመሳሰሉ እምነቶችም አንድ መሆን ይችላሉ። ይህንንም መደመር ሳይሆን መደነብ ነው የምለው።

ወገኖቼ ሆይ እግዚአብሔር በደመነፍ ከመነዳት ያውጣን።

"ፈጣሪያችን ሆይ እስራኤሎችን በተደጋጋሚ ይቅር እንዳልካቸው ልጆችህ ነንና ይቅር በለን!!!

አሜን አሜን አሜን

አንተነህ ጌትነት (የሶማው) ከባእድ ሀገር ሜልበርን አውስትራሊያ

አስተያየት ካላችሁ መዚህ ኢሜል ጻፉልኝ፡muluadamche@gmail.com